# በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት የከተማ ቦታ ኢንቨስትመንት

## አመራጭ እድሎች

መንግስት የሀገራችን ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ልማትና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚያረጋግጡ ለኑሮ አመቺና በኘላን የሚመሩ እንዲሆኑ በማድረግ የአካባቢያቸው የልማት ማዕከልና የዲሞክራሲ ተምሳሌት ሆነው እርስ በራሳቸው ተሳስረው አለም አቀፍ ተወዳዳሪነታቸው ጨምሮ ብልጽግናን ተጐናጽፈው የሚታዩ መሆን እንዲችሉ የሚያሥችል የከተማ ልማት ፖሊሲ ቀርጾ በየደረጃው ያለውን አካል በማሳተፍ እየተንቀሳቀሰ በመሆኑ የሀገራችን ከተሞች በተጨባጭ ፈጣን የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት እየተመዘገበባቸው ይገኛል፡፡

የክልላችን መንግስትም በክልሉ የሚገኙ ከተሞች የንግድና ኢንቨስትመንት ቀጠና፣ መሠረተ ልማት የተሟላላቸውና ለነዋሪዎቻቸው ምቹ ሆነው እንዲገኙ ለማስቻል የመመዘኛ መስፈርት በማዘጋጀት የከተሞችን ደረጃ ወሥኗል፤ የአቅም ግንባታና ሌሎችንም ተግባራት በማከናወኑ በተለይም በክልሉ የገበያ መዳረሻ /የሪፎርም/ ከተማ ሆነው የተካለሉ 22 ከተሞች በከፍተኛ ፍጥነት ተከታታይነት ያለው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እመርታ ማሥመዝገብ ችለዋል፡፡ እያሥመዘገቡም ይገኛሉ፡፡

የክልሉ መንግስት በ22ቱ የሪፎርም ከተሞችም ሆነ በሌሎች ታዳጊ ከተሞች ንጽጽራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ኢንቨስትመንቶች እንዲስፋፉ በፈጠረው ምቹ ሁኔታ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ባለሀብቶች እንዲገቡ አስችሏል፡፡ በየከተሞቹ በኢንቨስትመንቱ የተሠማሩ ባለሀብቶችም ራሳቸውን ከመጥቀም አልፈው ለበርካታ ዜጐች የሥራ እድል አሥገኝተዋል፤ የገጠርና የከተማ ትስስርም እንዲጠናከር የበኩላቸውን እየተወጡ ይገኛሉ፡፡

በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች አስፈላጊውን ለመደገፍ ቁርጠኛ አቋም ወስዶ እየተንቀሳቀሰ ያለው የክልሉ መንግስት በቀጣይም ያለፉ ጠቃሚ ልምዶችን በመቀመርና መሠራት ሲገባቸው ያልተሠሩ ተግባራትን በመለየት ተጠናክሮ ለመስራት ከመዘጋጀቱም በላይ በክልሉ ከተሞች የኢንዱስትሪ ዞኖችን በመለየት መሠረተ ልማት እንዲሟሉላቸው አድርጓል፤ ለከተማ ግብርና፣ ለመህበራዊ አገልግሎት፣ ለሆቴሎችና ቱሪዝም አገልግሎት ሊሆኑ የሚችሉ በቂ ቦታዎችን በጥናት በመለየት ጋይድ ማኘ እንዲዘጋጅላቸው አድርጓል፤ ከ300 በላይ የኢንዱስትሪ ኘሮጀክት ኘሮፋይሎች በአማካሪዎች ተጠንተው እንዲዘጋጅ አድርጓል፤ ግሮዝ ፖልና ግሮዝ ኮሪደሮችን ከልሏል፡፡ በዚህ ብቻ ሳይወሠን የተፈጠሩትን ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታዎች የአለም አቀፉ ማህበረሠብ ተገንዝቦ የልማት አጋሩ መሆን እንዲችል የተለያዩ የግንኙነት አግባቦችን ተጠቅሞ መረጃዎችን አሠራጭቷል፡፡ እያሠራጨም ይገኛል፡፡

በቀጣይ በክልላችን ባሉ ከተሞች በተለይ ባለኮከብ ደረጃ ያላቸውን ሆቴሎች፣ ከፍተኛ የትምህርትና የጤና ተቋማትን፣ ታላላቅ የጨርቃጨርቅና የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎችንና ታላላቅ ኢንዱስትሪዎችን የመገንባት ፍላጐትና አቅም ያላቸውን ልማታዊ ባለሀብቶች ቅድሚያ የሚስተናገዱበት ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ በመሆኑም ከላይ በዘረዘርናቸውም ሆነ በሌሎች የከተማ ኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሠማራት ፍላጐቱና አቅሙ ያላቸውን ልማታዊ ባለሀብቶች በመረጡት ቦታ ለመሥራት ቢመጡ በፍቅር ተቀብለን ለማስተናገድ ዝግጁነታችንን እየገለጽን ለበለጠ መረጃ በጋይድ ማኘ ተለክቶ የተዘጋጀውንና አልሚዎችን እየጠበቀ ያለውን የከተማ መሬት መረጃና የሚገኝበትን ቦታ ከቀጣዩ ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

# በከተሞች ለኢንዱስትሪ ልማት የተዘጋጀ መሬት

| ተ.ቁ | መሬቱ የሚገኝ በት ከተማው ስም | የተዘጋጀዉ መሬት የሚገኝበት ዞን | የተዘጋጀዉ መሬት በሄክታር | ያለ መሬት በሄ ክታር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀዋሳ | ሀዋሳ | 83.6 | 34.5 |
| 2 | ይርጋለም | ሲዳማ | 68 .4 | 53.9 |
| 3 | ሀላባ | ሀላባ | 45 | 43.5 |
| 4 | ዱራሜ | ከምባታ ጠምባሮ | 50 | 40 |
| 5 | ሶዶ | ወላይታ | 42 | 39.5 |
| 6 | አረካ | ወላይታ | 40 | 40 |
| 7 | ቦዲቲ | ወላይታ | 40 | 40 |
| 8 | አርባ ምንጭ | ጋሞጎፋ | 40 | 40 |
| 9 | ሳውላ | ጋሞጎፋ | 30 | 30 |
| 10 | ጂንካ | ደቡብ ኦሞ | 40 | 40 |
| 11 | ዲላ | ጌዴኦ | 50 | 50 |
| 12 | ይርጋጨፌ | ጌዲኦ | 12.5 | 12.5 |
| 13 | ቦንጋ | ካፋ | 40 | 33.5 |
| 14 | ቴፒ | ሸካ | 46 | 36 |
| 15 | ወልቂጤ | ጉራጌ | 50 | 50 |
| 16 | ቡታጅራ | ጉራጌ | 37 | 29.6 |
| 17 | ሚዛን አማን | ቤንች ማጂ | 44.5 | 44.5 |
| 18 | ሆሳዕና | ሀዲያ | 63 | 60 |
| 19 | ወራቤ | ሲልጤ | 21.1 | 11.1 |
| 20 | አለታወንዶ | ሲዳማ | 19.3 | 19.3 |

| ተራ ቁ. | ዞን/ ልዩ ወረዳ | መሬቱ የሚገኝበት ከተማ | የተዘጋጀ የመሬት መጠን በሄ/ር | ቦታው ቢሰጥ የሚችለው አገልግሎት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ወላይታ | ሶዶ | 40.06 | ለሆቴሎች ለሪልስቴት ጋራጅባንክ ነዳጅ ማደያ |
| | | ቦዲቲ | 10 | ሆቴል ሱፐርማረኬት ካፍቴሪያፔንስዮን ሱቅ |
| | | አረካ | 10 | ቡና ማድረቅያ ቆዳ ማድረቅያከብት ማድለብያ ሱቆች |
| | | ጠበላ | 2.4 | ሆቴል ሱፐርማረኬት ካፍቴሪያፔንስዮን ሱቅ |
| | | ገሱባ | 2.15 | ሆቴል ሱፐርማረኬት ካፍቴሪያፔንስዮን ሱቅ |
| | | በሌ | 2.15 | ሆቴል ሱፐርማረኬት ካፍቴሪያፔንስዮን ሱቅ |
| | | ጉኑኖ | 2.75 | ሆቴል ሱፐርማረኬት ካፍቴሪያፔንስዮን ሱቅ |
| | ድምር | | 69.51 | |
| 2 | ሲዳማ | ቀባዶ | 18 | ለእንዱስትሪና ለማህበራዊአገልግሎት |
| | | ይ/ዓለም | 40.1 | ለእንዱስትሪና ለማህበራዊአገልግሎት |
| | | ዳዬ | 6 | ለማህበራዊ አገልግሎት |
| | | አለታ ወንዶ | 10 | ለእንዱስትሪና ለማህበራዊአገልግሎት |
| | ድምር | | 74.1 | |
| 3 | አዋሣ | ባህል አዳራሽ | 0.15 | ለተለያየ አገልግሎት |
| | | ታቦር | 0.514 | ለተለያየ አገልግሎት ለሆቴልገስት ሀውስ |
| | | መናኸሪያ | 1.15 | ለፔንስዩን ክሊኒክ ገስት ሀውስ<br>ሪልስቴት ለተለያየ አገልግሎት |
| | ድምር | | 1.98 | |
| 4 | ከምባታ ጠምባሮ | ዱራሜ | 62.7 | እ/ዕርባታ ለሆቴል ለት/ቤት<br>ክሊኒክ ለሪልስቴት ለእንዱስትሪ ከ/ግብርና |
| | | ሺንሽቾ | 14.81 | ለሪልስቴት ለእንዱስትሪ ን/ማዕከል ለሆስፒታልና ለት/ቤቶች |
| | | ሀደሮ | 1.5 | ለአነስተኛ ኢንዱስትሪ (ለብሎኬት ማምረቻ) |
| | | አንገጫ | 15.97 | ለሆቴልና ለሞቴል አገ/ትለከተማ ግብርና |
| | | በሌሎች | 208.9 | ለሆቴልና ለሞቴል አገ/ት |
| | ድምር | | 303.88 | |

| ተራ ቁ. | ዞን/ ልዩ ወረዳ | መሬቱ የሚገኝበት ከተማ | የተዘጋጀ የመሬት መጠን በሄ/ር | ቦታው ሊሰጥ የሚችለው አገልግሎት |
|---|---|---|---|---|
| 5 | ጋሞ ጎፋ | አ/ምንጭ | 10.508 | ሪልስቴት ለባለኮከብ ሆቴልፔንስዩን ማ/አገልግሎት |
| | ድምር | | 10.508 | |
| 6 | ዳውሮ | ተርጫ | | ለሆቴል ለት/ት ማደያ ለጤና ተቋማት |
| | | ዋካ | 3.0 | ለሆቴል ማደያ ወዘተ |
| | ድምር | | 39 | |
| 7 | ደቡብ ኦሞ | ዲንካ | 5.3037 | ሪልስቴት ለባለኮከብ ሆቴል ለተለያየ አገልግሎት |
| | ድምር | | 44.3037 | |
| 8 | ሸካ | ማሻ | 1.2408 | ለሆቴል ለባንክ ለንግድ |
| | | ቴፒ | 5.3384 | ለፓርክ ለሆቴል ለንግድ |
| | ድምር | | 6.5792 | |
| 9 | ጉራጌ | አገና | 169.93 | ለማህበራዊ አገልግሎት ለሆቴልለ ከተማ ግብርና |
| | | ኬላ | 10.645 | ለተለያየ አገልግሎትኢንዱስትሪ |
| | | ቡኢ | 60.00 | ለተለያየ አገልግሎትኢንዱስትሪ |
| | | መሃል አምባ | 5.75 | ለተለያየ አገልግሎትኢንዱስትሪ |
| | | ቡታጅራ | 21..66 | ለተለያየ አገልግሎትኢንዱስትሪ |
| | | አረቅጥ | 5.6 | ለተለያየ አገልግሎትኢንዱስትሪ |
| | | ወልቂጤ | 6.75 | ለተለያየ አገልግሎትኢንዱስትሪ |
| | | ሃዋሪያት | 43.37 | ከተማ ግብር ሆቴልና ቱሪዝም |
| | | ጉንችሬ | 4.11 | ለማህበራዊ አገልግሎት ለሆቴል ኢንዱስትሪ |
| | | ጉንችሬ ማዞሪያ | 5.079 | ከተማ ግብር አግሮኢንዱስትሪ |
| | | ቀሴ | 54.94 | ለተለያየ አገልግሎት |
| | | እምድብር | 1.93 | ለተለያየ አገልግሎት |
| | ድምር | | 389.9886 | |
| 10 | ሀዲያ | ሆሜዕና | 25.33 | ለእንዱስትሪ ለማህበራዊአገልግሎትና ለሪልስቴት |
| | | ሾኔ | 10.8 | ለማህበራዊአገልግሎትና ለሪልስቴት |
| | | ጊምብቹ | 0.5 | ለማህበራዊአገልግሎትና ለሪልስቴት |
| | ድምር | | 36.63 | |

| ተራ ቁ. | ዞን/ ልዩ ወረዳ | መሬቱ የሚገኝበት ከተማ | የተዘጋጀ የመሬት መጠን በሄ/ሬ | ቦታው ሊሰጥ የሚችለው አገልግሎት |
|---|---|---|---|---|
| 11 | ከፋ | ቦንጋ | 21.1499 | ለአግሮኢንዱስተሪ ልማት ለማህበራዊአገልግሎት |
| | ድምር | | 21.1499 | |
| 12 | ጌዴኦ | ዲላ | 12.43 | ለሆቴል ለሪልስቴት ለገበያ ማዕከል |
| | | ጨለለቅጡ | 4.5 | ለኢንዱስትሪ ለሆቴል ለመዋዕለ ህፃናት |
| | | ይ/ጨፌ | 0.1859 | ለገበያ ማዕከል ለሆቴል ለሪልስቴት |
| | | ገደብ | 4.2 | ለኢንዱስትሪ ሆቴልናለት/( |
| | | ፍ/ገነት | 3.1537 | ለአፀደ ህፃናት ለማደያ ለኢንዱስትሪ ለከብት እርባታ |
| | | ቡሌ | 23.10 | ለአፀደ ህፃናት ለሆቴል |
| | | ወናጎ | 6.0 | ለሆቴል ለኢንዱስትሪ ለከብት እርባታ |
| | ድምር | | 53.5696 | |
| 13 | ስልጤ | ወራቤ | 24.1 | ለኢንዱስትሪ አገ/ሎት |
| | ድምር | | 24.1 | |
| 14 | አላባ | አላባ | 25.75 | ለተለያየ አገልግሎት ለንግ. ለከብት እርባታ |
| | ድምር | | 25.75 | |
| 15 | ባስኬቶ | ላስካ | 0.1356 | ለሆቴልና ሬስቶራንት |
| | ድምር | | 0.1356 | |